**አጠቃላይ ርዕስ፦**

**የእግዚአብሔር ፈቃድ—አንድ ማንነት፣ አንድ መንገድ እና አንድ ግብ**

መልዕክት አንድ

**በእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ እውቀት መሞላት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤፌ. 1፡5፣ 9፣ 11፤ ራእ. 4፡11፤ ቆላ. 1፡9፤ 4፡12

I. **የእግዚአብሔር ፈቃድ የእግዚአብሔር ምኞት ነው፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱ ማድረግ የሚፈልገው ነገር ነው—ኤፌ. 1፡9።**

II. **የእግዚአብሔር በጎ ደስታ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ በጎ ደስታው በፈቃዱ ውስጥ ተካቷል፣ ስለዚህ ፈቃዱ መጀመሪያ ይመጣል—ቁ. 5።**

III. **የእግዚአብሔር ፈቃድ አላማውን ለመፈጸም ያለው ቁርጠኝነት ነው—ቁ. 11፤ 1 ቆሮ. 1፡1።**

IV. **እግዚአብሔር የራሱ ደስታ ፈቃድ ያለው የአላማ አምላክ ነው፣ አላማውን ያከናውን እና ይፈጽም ዘንድ ሁሉንም ነገሮች ስለ ፈቃዱ ፈጥሮአል—ራእ. 4፡11፤ ኤፌ. 3፡9-11፤ ቆላ. 1፡9፦**

   ሀ. የእግዚአብሔር ፈቃድ የልቡ መሻት፣ ከሰው ጋር መዋሐዱ እና ዘላለማዊ እቅዱ መፈጸሙ ነው—ኤፌ. 1፡5፣ 9፣ 11፤ 5፡17።

   ለ. የእግዚአብሔር ፈቃድ ሙላቱ፣ መገለጡ እንዲሆን ለክርስቶስ አካል ማግኘት ነው—ሮሜ. 12፡2፣ 5፤ ኤፌ. 1፡5፣ 9፣ 11፣ 22-23።

V. **ቆላስይስ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ [የሚናገር] መጽሐፍ ነው—1፡9፤ 4፡12፦**

   ሀ. በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ፈቃድ በትንንሽ ነገሮች ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም—ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ፈቃድ፣ ታላቁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

   ለ. ቆላስይስ በመሻቱና በአላማው መሠረት እግዚአብሔር በመላው አጽናፍ-ዓለም፣ በፍጥረት፣ በቤዛነት ውስጥ፣ በሚመጣው ዘመን እና በዘላለም ውስጥ ያለው አላማ ምን እንደሆነ ይገልጣል።

VI. **በእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ እውቀት መሞላት ያስፈልገናል—ቆላ. 1፡9፦**

   ሀ. በቆላስይስ 1፡9 ላይ ያለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ዘላለማዊ አላማውን በተመለከተ ያለው ፈቃዱ፣ ስለክርስቶስ የሆነውን ኢኮኖሚውን በተመለከተ ነው—ኤፌ. 1፡5፣ 9፣ 11።

   ለ. የእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ እውቀት ያለን መሆን እግዚአብሔር በአጽናፍ-ዓለም ሊያደርግ ያቀደውን እናውቅ ዘንድ የእግዚአብሔር እቅድ መገለጥ ያለን መሆን ማለት ነው—ራእ. 4፡11፦

      1. የእግዚአብሔር እቅድ በመለኮታዊው ኢኮኖሚ ውስጥ ክርስቶስን ሁሉ ነገር ማድረግ ነው—ማቴ. 17፡5፤ ቆላ. 1፡15-18፤ 3፡10-11።

      2. የእግዚአብሔር እቅድ መገለጥ ብዙ የክርስቶስ ልምምድ እንዲኖረን መንገድ ይከፍትልናል—2፡16-17፤ 3፡4፣ 15-16።

   ሐ. የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእኛ ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስን እንድናውቀው፣ እንድንለማመደው እና እንደ ሕይወታችን እንድንኖረው ነው—1፡9፣ 15-18፤ 3፡4።

   መ. ለጌታ እንደሚገባ መመላለስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ እውቀት ያለው ከመሆን የሚመጣ ነው፤ እንዲህ ያለው ምልልስ ክርስቶስን የምንኖርበት ምልልስ ነው—1፡10፤ ፊልጵ. 1፡19-21።

VII. **በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ የበሰሉ (ፍጹማን) ሆነን እና ተረድተን (ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆነን) ልንቆም ያስፈልጋል—ቆላ. 4፡12።**

መልእክት ሁለት

**አንድ ማንነት—ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ቆላ. 1፡9፣ 12፣ 15-18፣ 27፤ 2፡2፣ 8-9፣ 16-17፤ 3-4፣ 10-11፣ 15

I. **የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ውስጥ፣ በክርስቶስ ላይ ያተኮረ እና ለክርስቶስ ነው፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ክርስቶስ ሁሉ ነገር ነው—1፡9።**

II. **በቆላስይስ ውስጥ የተገለጠው ክርስቶስ ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው፣ ፊተኛ ስፍራ ያለው፣ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከላዊነት እና አጽናፍ-ዓለማዊነት የሆነው ነው—ቁ. 15-18፣ 27፤ 2፡16-17፤ 3፡4፣ 10-11፦**

ሀ. ቆላስይስ ሁሉን-ያካተተውን—አምላክ፣ ሰው እና በአጽናፍ-ዓለም ያለ አዎንታዊ ነገር ሁሉ እውነታ የሆነውን—ክርስቶስ ይገልጣል—2፡9፣ 16-17።

ለ. ክርስቶስ የመጀመሪያው ፍጥረት እና የአዲሱ ፍጥረት በኵር መሆኑ ማለት እርሱ ሁሉን-ያካተተ እና ሁሉን-ደረስ ነው ማለት ነው—1፡15፣ 18።

ሐ. ክርስቶስ ፊተኛው፣ በነገር ሁሉ የመጀመሪያ ስፍራ ያለው ነው—ቆላ. 1፡18።

መ. ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማዕከላዊነት እና አጽናፍ-ዓለማዊነት፣ ማዕከል እና የከበብ ዳርቻ ነው—ማቴ. 17፡5፤ ቆላ. 1፡15-27፤ ኤፌ 1፡10።

III. **የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ እድል ፈንታችን እንዲሆን ነው—ቆላ. 1፡9፣ 12፦**

ሀ. በ 1፡9 ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ክርስቶስን ያመለክታል፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነውን ክርስቶስ ከማወቃችን፣ ከመለማመዳችን እና ከመኖራችን ጋር በተገናኘ ጥልቅ ነው።

ለ. የእግዚአብሔር ፈቃድ ክርስቶስን እንድናውቅ፣ ክርስቶስን እንድንለማመድ፣ ክርስቶስን እንድንደሰት፣ በክርስቶስ ፈጽመን እንድንሞላ እና ክርስቶስ ሕይወታችን እና ማንነታችን እንዲሆን ነው—3፡4።

IV. **ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ እንደ የክብር ተስፋችን በውስጣችን ያድራል—ቆላ. 1፡27።**

V. **ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ ሕይወታችን ነው—ቆላ. 3፡4፦**

ሀ. *ሕይወታችን* የሚለው አገላለጽ የአዎንታዊ ነገር ሁሉ እውነታ የሆነውን ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ እንደምንለማመደው የሚያሳይ ጠንካራ ምልከታ ነው—2፡16-17።

ለ. ክርስቶስ ሕይወታችን ስለሆነ፣ እርሱ ያለው ሁሉ እና እርሱ የደረሰበት እና ያገኘው ነገር ሁሉ ለእኛ ውስጠ-ልምምዳዊ ሆኗል—ሮሜ 8፡34፣ 10።

VI. **ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ የአንዱ አዲሱ ሰው ልዩና ብቸኛ ቅንብር ነው—ቆላ. 3፡10-11፦**

ሀ. አዲሱ ሰው የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ይዘት ክርስቶስ ብቻ ነው፤ በአዲሱ ሰው ውስጥ ስፍራ ያለው ለክርስቶስ ብቻ ነው፣ ምክንያቱም እርሱ እያንዳንዱ ሰው እና በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ነውና።

ለ. አዲሱ ሰው በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክርስቶስ ውስጥ፣ በክርስቶስ በኩል እና ለክርስቶስ ነን፣ በክርስቶስ ውስጥ የእግዚአብሔር መገለጥ ለመሆን በክርስቶስ ተጋጥመናል—1፡16-17።

VII. **ሁሉን-ያካተተው፣ ሁሉን-ደረስ የሆነው ክርስቶስ ሰላማችን ነው—ቁ. 20፤ 3፡15።**

መልእክት ሦስት

## አንድ መንገድ—የክርስቶስ መስቀል

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል:- ቆላ. 1፡20-22፤ 2፡11-15

**I. ክርስቶስ፣ ልዩና ብቸኛው ማንነት ከሁሉ ነገሮች በተጻራሪ ነው፣ መስቀሉ፣ ልዩና ብቸኛው መንገድ ከሁሉ መንገዶች በተጻራሪ ነው—ቆላ. 1፡20።**

**II. አንዱ ማንነት—ክርስቶስ—የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል ነው፣ አንዱ መንገድ—መስቀሉ—የእግዚአብሔር አገዛዝ ማዕከል ነው—1 ቆሮ. 2፡2፤ 1፡17-18፣ 23፤ ገላ. 6፡14:-**

ሀ. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በመስቀሉ ይገዛል እንዲሁም ሁሉንም ነገር በመስቀሉ ያስወግዳል—ቆላ. 1፡20፤ 2፡14-15።

ለ. እግዚአብሔር በአጽናፍ-ዓለም ውስጥ ያሉትን አሉታዊ ነገሮችን ሁሉ በመስቀሉ አስወግዷል፣ አሁንም ሁሉንም ነገር በመስቀሉ በኩል እየገዛ ነው—ኤፌ. 2፡14-16።

**III. የቆላስይስ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ክርስቶስ ሁሉም እና በሁሉም ውስጥ መሆን እንዳለበት ያስተምራል፤ ክርስቶስ ያልሆነው ነገር ሁሉ ወደ መስቀሉ መሄድ አለበት:-**

ሀ. በመስቀሉ በኩል ምንም መሆን፣ ምንም የሌለን እና ምንም ማድረግ የማንችል መሆን ያስፈልገናል።

ለ. መስቀሉን ካስወገድነው፣ የሆንነው፣ ያለን እና ማድረግ የምንችለው የክርስቶስ ምትክ ይሆናል—1 ቆሮ. 1፡17-18፣ 23።

**IV. "በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ"—ቆላ. 1፡20:-**

ሀ. የመላእክት አለቃ ከሆነው ሰይጣን እና እርሱን ከተከተሉት መላእክት አመጽ የተነሣ፣ ሰማያት ተበክለው ነበር፤ ስለዚህ፣ በምድር ላይ ያሉ ነገሮች ብቻ ሳይሆኑ በሰማያት ያሉ ነገሮችም ጭምር ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ያስፈልጋቸው ነበር—ቁ. 20።

ለ. እንደ ኃጢአተኞች ቤዛነት አስፈልጎናል፣ እንደ ጠላቶች ደግሞ መታረቅ አስፈልጎናል—ቁ. 14፣ 21-22።

**V. "በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል"—2፡14:-**

ሀ. *ትእዛዛት* የሚያመለክተው [በሙሴ የተሰጡ] ድንጋጌዎችን ከስርዓታቸው ጋር ነው፣ እነዚህም የአኗኗር እና የአምልኮ መልኮች ወይም ዘይቤዎች ናቸው።

ለ. *በመስቀል ጠርቆ* ማለት በአዋጅ የተነገሩትን የትእዛዛትን ሕግ መሻር ማለት ነው።

**VI. "አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፣ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው"—ቆላ. 2፡15:-**

ሀ. ክርስቶስን፣ እግዚአብሔርን እና ክፉ የመላእክት አለቆችን እና ሥልጣናትን የሚያካትቱ ተግባሮች በመስቀል ላይ ወደ ትኩረት እንዲመጡ ተደርገዋል፤ ስለዚህ፣ መስቀሉ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ፣ ማዕከላዊ እና ልዩና ብቸኛ መንገድ ሆኗል—ቁ. 14-15:-

1. በስቅለቱ ክርስቶስ ቤዛነትን ለመፈጸም ተግቶ ሠርቷል፣ እግዚአብሔር አብም በኃጢአት ላይ ለመፍረድ እና ሕጉን በመስቀል ላይ ለመቸንከር እየሠራ ነበር—ቁ. 14።
2. በተመሳሳይ ጊዜ፣ ክፉ አለቆች እና ሥልጣናት ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ክርስቶስ ገፍተው በመቅረብ የእግዚአብሔርን እና የክርስቶስን ሥራ ለማስተጓጎል በነበራቸው ሙከራ ተጠምደው ነበር።

ለ. እግዚአብሔር የክፉ መላእክት አለቆችን እና ሥልጣናትን በማሳፈር በመስቀል ላይ በግልጥ (በገሃድ) እንዲታዩ አደረጋቸው፣ [በመስቀሉም] ድል ነሣቸው—ቁ. 15።

መልእክት አራት

## አንድ ግብ—ቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ አካል

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ቆላ. 1፡18፤ 2፡19፤ 3፡15፤ 4፡15-16

**I. ክርስቶስ የአካሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው—ቆላ. 1፡18፦**

ሀ. ቤተ ክርስቲያን ከሦስታንዱ አምላክ እና ከተመረጡና ከተዋጁ ሕዝቡ የተቀናበረች አካል የሆነች፣ የክርስቶስ አካል መሆኗን ማየት አለብን—ኤፌ. 1፡22-23፤ 4፡4-6።

ለ. አካሉ የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ነው፤ አካሉ ባይኖር ኖሮ፣ ቤተ ክርስቲያን ስሜት የማትሰጥ እና ትርጉም የሌላት ትሆን ነበር—1 ቆሮ. 12፡12፤ 27፤ 1፡2።

ሐ. ክርስቶስ ራስ እንደሆነ እና እኛ የአካሉ ብልቶች እንደሆንን መገንዘባችን በጣም አስፈላጊ ነው—ቆላ. 1፡18፤ 2፡19፤ ኤፌ. 4፡15-16፦

1. በአካሉ ውስጥ መኖር በአካሉ ራስ ሥር ከብልቶቹ ሁሉ ጋር በጋራ መኖር ነው።
2. የአካሉን ሕይወት ለመኖር፣ በአካሉ ራስ ሥር መሆን እና የአካሉን ራስ እንደ ሕይወታችን፣ እንደ ዋናው ነገር እና እንደ የመላው ማንነታችን ማዕከል መውሰድ አለብን—ቆላ. 1፡18፤ 2፡19።
3. በክርስቶስ አካል ውስጥ የመኖር የመጀመሪያው መርህ ለአካሉ ራስ ሥልጣን መታዘዝ ነው—ኤፌ. 4፡15፦
   ሀ. ክርስቶስ የአካሉ ራስ ነው፣ ሕይወት በነጻነት መፍሰስ የሚችለው እርሱ ሙሉ ቁጥጥር ሲኖረው ነው—ቁ. 16።
   ለ. አካሉ ወደ ራሱ ያለው ብቸኛ ግዴታው ያለ ምንም አመለካከት፣ ሃሳብ እና አስተያየት መታዘዝ እና መገዛት ነው።

**II. አካሉ በእግዚአብሔር ማደግ ያድጋል—ቆላ. 2፡19፦**

ሀ. የአካሉ እድገት በውስጣችን ባለው የእግዚአብሔር ማደግ፣ የእግዚአብሔር መደመር፣ የእግዚአብሔር መጨመር ላይ ይመረኮዛል—ኤፌ. 4፡16።

ለ. እግዚአብሔር እድገትን የሚሰጠው ውስጠ-ልምምዳዊ በሆነ መንገድ ራሱን ለእኛ በመስጠት ነው—3፡16-17፦

1. እግዚአብሔር ለእኛ እድገትን መስጠቱ ማለት ራሱን ይሰጠናል ማለት ነው—1 ቆሮ. 3፡6-7።
2. እግዚአብሔር ወደ እኛ አብዝቶ ሲጨመር፣ ብዙ እድገት ይሰጠናል—ኤፌ. 4፡15-16።

**III. በአንዱ የክርስቶስ አካል ውስጥ ክርስቶስ ራሱ ወደሆነው ወደ የክርስቶስ ሰላም ተጠርተናል—ቆላ. 3፡15፦**

ሀ. ክርስቶስ የሚለያዩትን የሕግ ትእዛዛት (ድንጋጌዎች) በሥጋው በመሻር፣ ማለትም፣ ጠላትነትን በመግደል፣ እና የአይሁድ እና የአሕዛብን አማኞች አንድ አዲስ ሰው አድርጎ በመፍጠር፣ በአማኞች ሁሉ መካከል ሰላም ተደርጓል—ኤፌ. 2፡15።

ለ. ለአካሉ ሕይወት የክርስቶስ ሰላም ከአካሉ ብልቶች ጋር ባለን ግንኙነት በልባችን ባሉት ነገሮች ሁሉ ላይ እንዲወስን መፍቀድ አለብን—ቆላ. 3፡15።

**IV. እንደ የአካሉ ብልቶች የአካሉ ንቃተ-ሕሊናዊ ግንዛቤ ሊኖረን እና ለአካሉ ስሜት ሊኖረን ያስፈልጋል—1 ቆሮ. 12፡25-26፤ ሮሜ 12፡15፦**

ሀ. እንደ ጳውሎስ፣ የአካሉን ራስ ስሜት እንደ የገዛ ራሳችን ስሜት መውሰድ አለብን፤ ይህ በአካሉ ሕይወት ውስጥ ለመኖራችን የግድ አስፈላጊ ነው—ፊልጵ. 1፡8።

ለ. የምናደርገው ነገር ሁሉ አካሉን ይመለከታል፤ ስለዚህ፣ በምናደርገው ነገር ሁሉ አካሉን በአእምሮአችን፣ በአስተሳሰቦቻችን፣ በቃሎቻችን እና በድርጊቶቻችን ውስጥ እንዳለ አገዛዝ በመውሰድ ለአካሉ ግድ መሰኘት አለብን—1 ቆሮ. 12፡12-27፤ 2 ቆሮ. 8፡21።

**V. ልዩና-ብቸኛው የክርስቶስ አካል በብዙ አጥቢያዎች እንደ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ይገለጣል—ቆላ. 4፡15-16፤ ኤፌ. 4፡4፤ ራእ. 1፡4፣ 11፦**

ሀ. አንዱ አካል በብዙ አጥቢያዎች እንደ ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የሚገለጥ አንዱ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው—ማቴ. 16፡18፤ 18፡17፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 2፡21-22፤ 1 ቆሮ. 1፡2፤ 12፡27።

ለ. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በአንድ በተወሰነ አጥቢያ ውስጥ ያለች የክርስቶስ አካል መገለጥ ናት—1 ቆሮ. 1፡2፤ 10፡32፣ 17፤ 12፡12-13፣ 20፣ 27።